

# በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

# ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

## ከጃንዋሪ 21-31 የነበረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

## እንዲሁም

## ከፌብርዋሪ 1-10፣11-20 የሚኖረዉ የአየር ሁኔታ ትንበያ እና

## ምክረ ሃሳብ

ፌብርዋሪ 2026

አዲስ አበባ

ስልክ+251115538394ፋክስ 0115517066 ኢሜይል፡emi@ethiomet.gov.et ዌብ ሳይት www.ethiomet.gov.et

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣
## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ


### 1. እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ

በጃንዋሪ ሶስተኛው አሥራ አንድ ቀናት በአንዳንድ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ፤ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ አመዝኖባቸው ተስተውሏል፡፡ በተለይም የሰሜን ምሥራቅ፣ መካከለኛው፣ ምሥራቅ እና ደቡብ ደጋማ የሀገሪቱ ክፍሎች ደረቅ፣ ፀሐያማና ነፋሻማ የአየር ሁኔታ ነበራቸው። ከዚሁ ጋር ተያይዞ የሌሊትና የማለዳው ቅዝቃዜ አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናቶች በተዳከመ ሁኔታ የተስተዋለ ሲሆን፤ በጥቂት የሀገሪቱ ደጋማ ሥፍራዎች ላይ የቀኑ ዝቅተኛ የሙቀት መጠን ከ5 ዲግሪ ሴልሽየስ በታች ሆኖ ተመዝግቧ (ምስል 1)፡፡ ለአብነትም ቁሉቢ 4.0፣ 3.8፣ 3.6፣ 3.5፣ 3.1፣ 2.3፣ 2.0፣ 2.0፣ 2.2፣ ጎብዬሬ 4.8፣ ቡሂ 4.0፣ 4.0፣ኮረም 4.5፣ 4.5፣ 4.0፣ ጨለንቆ -1.0፣ 2.0፣ 2.2፣-1.0፣1.0፣-1.0፣1.0፣ አምባ ማሪያም 4.0፣ 4.8፣4.5፣ ጅግጅጋ 4.5፣ 3.0፣ ሐሮማያ 4.6 እና አርሲ ሮቤ 4.5 በዲግሪ ሴልሽየስ ተመዝግቧል፡፡


በሌላ በኩል አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናት ለዝናብ መፈጠር ምቹ የሆኑ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ነበራቸው፡፡ ከዚህ ጋር ተያይዞ የደቡብ አጋማሽ እና የደቡም ምዕራብ የሀገሪቱ ስፍራዎች ላይ የተሸላ የደመና ሽፋን ነበራቸዉ፡፡ በተጨማሪም በፀሀይ ኃይል ታግዞ ከተፈጠረው ዝናብ ሰጪ ደመናዎች ጋር ተያይዞ በጥቂት የደቡብ ምዕራብ የሀገሪቱ አካባቢዎች በ24 ሰዓት ዉስጥ ከ3 ሚ.ሜ በላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ ተመዝግቦባቸዋል፡፡ በ24 ሠዓት ዉስጥ ከ5 ሚ.ሜ በላይ አነስተኛ መጠን ከተመዘገበባቸው የሚቲዎሮሎጂ ጣቢያዎች መካከል ደብረ ማርቆስ 21.5፣ ጎሬ 10.5፣ 12.2፣ ጅማ 14.0፣ 7.8፣ ብላቴ 7.8፣ ጭራ 5.9፣ ፍቼ 7.3፣ ጋቲራ 5.3፣ 14.7፣ 17.3፣ ጉንዶ መስቀል 6.0፣ እምድብር 8.5፣ 15.5፣ ሶኮሩ 5.7፣ ተርጫ 10.0፣ ወላይታ ሶዶ 5.1፣ ኮሶ በር 9.3፣ ይርጋለም 16.2 እና ጋሳይ 9.5 ሚ.ሜ ይገኙበታል፡፡

ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በጥቂት የሀገሪቱ አከባቢዎች የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከቦታ ሽፋን አንፃር ሲገመገም ከ6-40 ሚ.ሜ የሚደርስ ዝናብ ከ1-5 ቀናት ያህል ዝናብ ነበራቸዉ (ካርታ 1 እና 2)፡፡በአጠቃላይ ባለፉት አስራ አንድ ቀናት የዘነበዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር በጋ ሁለተኛ የዝናብ ወቅታቸዉ በሆኑት የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ በአብዛኛዉ ከመደበኛዉ በታች የዝናብ መጠን ተመዝግቧል (ካርታ 3)፡፡


Ethiopian Meteorology Institute




ካርታ 1 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 ድረስ የነበረው የዝናብ መጠን በሚ.ሜ





ካርታ 2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 ድረስ ዝናብ የዘነበባቸዉ ቀናት



ካርታ 3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 1 እስከ 31/2025 የነበረዉ የዝናብ መጠን ከመደበኛዉ ጋር ሲነፃፀር

## 1.2 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በግብርና ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ


ባለፉት አስራ አንድ ቀናት በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የበጋው ደረቅ የእርጥበት ሁኔታ አመዝኖ እንደነበረ የተተነተኑ የግብርና ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመለክታሉ። ይህም ሁኔታ የመኸር አብቃይ በሆኑት የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ የድህረ ሰብል ስብሰባ ተግባራትን በተሟላ መልኩ ለማጠናቀቅ አመቺ ሁኔታን የፈጠረ ነበር። ከደረቃማውና ነፋሻማው የአየር ሁኔታ ጋር ተያይዞ የሌሊት እና የማለዳው ቅዝቃዜ በተለይም በአንዳንድ የሰሜን፣ የሰሜን ምስራቅ፣ የምዕራብ፣ የመካከለኛው እና የምስራቅ የሀገሪቱ ደጋማ ስፍራዎች ላይ በአንጻራዊ መልኩ ቅዝቃዜ የተስተዋለ ቢሆንም በሰብሎች ሁለንተናዊ እድገት ላይ ግን የጎላ ተጸዕኖ አልነበረውመ። በሌላም በኩል አልፎ አልፎ በነበሩት ቀናቶች በጥቂት የምዕራብ፣ የመካከለኛው እና የደቡብ የሀገሪቱ ኪስ ቦታዎች ላይ የነበረው እርጥበት ለቋሚ ተክሎችና የበልግ ወቅት እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ለማሳ ዝግጅት ጠቀሜታ ነበረው (ካርታ 4) ፡፡




ካርታ 4 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 1.3 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025 የነበረው የአየር ሁኔታ በውሃው ዘርፍ ላይ ያሳደረው ተፅዕኖ

ባሳለፍናቸው ጃንዋሪ ሶስተኛ አሥራ አንደ ቀናት አብዛኛዎቹ የሀገሪቱ ተፋሰሶች ደረቅ ሁኔታ ስር እንደነበሩ የተተነተኑ የውሃ ሚቲዎሮሎጂ መረጃዎች ያመላክታሉ። ሆኖም በጥቂት የመካከለኛ ኦሞ ጊቤ፣ የላይኛው ዋቢ ሸበሌ እና በጥቂት በመካከለኛው አባይ ተፋሰሶች ላይ የገጸ ምድር እርጥበት የነበራቸው ሲሆን ይህም ሁኔታ ለውሃ ሀብት መሻሻል መጠነኛ አስተዋፅዖ ነበረው፡፡ በሌላ በኩል አብዛኛው የአባይ፣ የተከዜ፣ የአዋሽ፣ የስምጥ ሸለቆ፣ የዋቤ ሸበሌ፣ የአይሻ፣ የመረብ ጋሽ እና የኦጋዴን ተፋሰሶች፣ የበጋው ደረቅ ሁኔታ ስር ቆይተው ነበር (ካርታ 5)።





ካርታ 5 እ.ኤ.አ ከጃንዋሪ 21 እስከ 31/2025
ድረስ የነበረው የእርጥበት ሁኔታ

## 2. መግቢያ


የፌብርዋሪ ወር በመደበኛ ሁኔታ የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት ጊዜ ነው፡፡ በተለይም ከወሩ አጋማሽ በኋላ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች እየተጠናከሩ ከመሄዳቸው ጋር ተያይዞ የደቡብ ምዕራብ፣ ደቡብ፣ ሰሜን ምሥራቅ፣ የምሥራቅ፣ የመካከለኛውና አጎራባች የስምጥ ሸለቆ ሥፍራዎች የተለያየ መጠን ያለው ዝናብ ያገኛሉ፡፡ በመደበኛ ሁኔታ በፌብርዋሪ የመጀመሪያው አሥር ቀናት በደቡብ ምዕራብና በደቡብ የሀገሪቱ ክፍሎች ላይ ከሚስተዋለው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት በስተቀር በአብዛኛው የሀገሪቱ ክፊሎች ላይ ደረቃማው የአየር ሁኔታ ያመዝናል፡፡

### 2.1 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1-10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ ትንበያ

በፌብርዋሪ የመጀመሪያዎች አሥር ቀናት ለዝናብ መፈጠር አስተዋጽኦ ሊያደርጉ የሚችሉ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ቀስ በቀስ እየተጠናከሩ እንደሚሄዱ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁ ጋር ተያይዞ ለዝናብ መፈጠር ምቹ ሁኔታን የሚፈጥሩ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች አልፎ በሚኖሩት ቀናቶች ላይ የተሻለ ገፅታ ይኖራቸዋል (ካርታ 6)፡፡ በተለይም የስምጥ ሸለቆ እና አዋሳኝ አካባቢዎች፣ የመካከለኛውና የደቡብ ምዕራብ አካባቢዎች ላይ የደመና ሽፋን እንደመጨምር ይጠበቃል፡፡ በተጨማሪም ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ አነስተኛ መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖረው አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ (ካርታ 1)፡፡ በሌላ በኩል በጋምቤላ፤ በሰሜን ምዕራብ፤ በሰሜን ምስራቅና በደቡብ ምስራቅ አከባቢዎች ላይ የቀኑ ከፍተኛ የሙቀት መጠን ከ 29 ዲግሪ ሴልሺየስ በላይ እንደሚሆን የትንበያ መረጃዎች ያሳያሉ (ካርታ 7)።




ካርታ 6 እ.ኤ.አ. 1 ከፌብርዋሪ 1-10/2026, የሚኖረዉ የዝናብ መጠን በሚ.ሜ




ካርታ 7 እ.ኤ.አ. 1 ከፌብርዋሪ 1-10/2026 የሚኖረዉ ከፍተኛ የሙቀት መጠን በዲ.ሴ

## በኢትዮጵያ የሚቲዎሮሎጂ ኢንስቲትዩት የሚቲዎሮሎጂ ትንበያ፣

## ቅድሚያ ማስጠንቀቂያ እና ምክር አገልግሎት ምርምር ዘርፍ

ሠንጠረዥ 1፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎችና በ24 ሰዓት ዉስጥ የሚኖረዉ የዝናቡ መጠን

| በጥቂት ቦታዎቻቸዉ ላይ አነስተኛ መጠን ዝናብ የሚያገኙ አከባቢዎች | | |
|---|---|---|
| ክልል | ዞን | የሚኖረዉ የዝናብ መጠን |
| ኦሮሚያ | ኢሉባቦር፣ ጅማ እና ቡኖ በደሌ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| አማራ | የደቡብ እና የሰሜን ወሎ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ | የሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ እና ሸካ ዞኖች | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ደቡብ ኢትዮጵያ | የወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞ፣ ጌዲዮ፣ | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |
| ሲዳማ | | አነስተኛ መጠን (ከ1-10 ሚ.ሜ) |

### 2.2 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 11 እስከ 20/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ አዝማሚያ

በመደበኛ ሁኔታ የፌብርዋሪ ሁለተኛው አሥር ቀናት የበልግ ዝናብ የሚጀምርበት እና የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች የሚጠናከሩበት ጊዜ ነው፡፡ ስለሆነም የደቡብ ምዕራብ፣ የመካከለኛው፣ የሰሜን ምሥራቅና የምሥራቅ የሀገሪቱ ክፍሎች ዝናብ ማግኘት ይጀምራሉ፡፡ በመጪዎቹ የፌብርዋሪ ሁለተኛ አሥር ቀናት አሁን እየተስተዋለ ያለዉ ዝናብ ሰጭ የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች በአብዛኛዎቹ የሀገሪቱ አካባቢዎች ላይ ቀጣይነት እንደሚኖረዉ የትንበያ መረጃዎች ይጠቁማሉ፡፡ ከዚሁም ጋር ተያይዞ ከሚጠናከሩት የሚቲዎሮሎጂ ገጽታዎች ላይ በመነሳት በተለይም በደቡብ ምዕራብ፣ በመካከለኛ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገራችን አከባቢዎች ላይ ቀላል መጠን ያለው ዝናብ እንደሚኖራቸዉ አሃዛዊ የትንበያ መረጃዎች ፡፡

## 2.3 እ.ኤ.አ ከፌብርዋሪ 1 እስከ 10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በግብርናው ሥራ እንቅስቃሴ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ የመጀመሪያዉ አስር ቀናት በደቡብ ምዕራብ እና በሰሜን ምስራቅ የሀገሪቱ አከባቢዎች ላይ የሚጠበቀው አነስተኛ መጠን ያለው እርጥበት ለቋሚ ተክሎች የውሃ ፍላጎት መሟላትና ለአርብቶ አደርና ከፊል አርብቶ አደር አካባቢዎች የግጦሽ ሳርና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ከማሻሻል አንፃር አዎንታዊ ሚና ይኖረዋል፡፡ በተጨማሪም የበልግ ወቅትን ቀድመው ለሚጀምሩ አካባቢዎች ማሳን አስቀድሞ ለማዘጋጀት ጠቀሜታ ይኖረዋል፡፡ በመሆኑም የሚኖሩ ስጋቶችን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የግብርና ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 2፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በግብርናው እንቅስቃሴ ላይ

| የመኸር ሰብል አብቃይና የበልግ እርሻ እንቅስቃሴን ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዞኖች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የተሰጠ ምክረ ሃሳብ |
| የኢሉባቦር፣ ጅማ ፣ቡኖ በደሌ ፣ የደቡብ እና ሰሜን ወሎ፣ ሸኮ፣ ከፋ፣ ኮንታ፣ ዳውሮ፣ ቤንች ሸኮ፣ ሸካ፣ ወላይታ፣ ጎፋ፣ ጋሞና ጌዲዮ ዞኖች | • አነስተኛ መጠን ያለዉ እርጥበት | • ለበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ቀድሞ የማሳ ዝግጅት ለማከናወን<br>• ለቋሚ ተክሎች ዕድገት<br>• የግጦሽ ሳር እና የመጠጥ ውሃ አቅርቦትን ለማሻሻል | • ለሰብል መዝራት በቂ ያለሆነ እርጥበት<br>• ተከታታይ ደረቅ ሰሞናት<br>• ከፍተኛ ትነት | • የበልግ እርሻ እንቅስቃሴ ቀድመው የሚጀምሩ አካባቢዎች የሚገኘውን እርጥበት በአግባቡ መጠቀም |

## 2.4 እ.አ.አ ከፌብርዋሪ 1-10/2026 የሚኖረው የአየር ሁኔታ በውሃ ዘርፍ ላይ ሊያሳድር የሚችለው ተፅዕኖ

በሚቀጥሉት የፌብርዋሪ የመጀመርያ አስር ቀናት በጥቂት ተፋሰሶች ላይ ዝቅተኛ የሆነ የገፀ ምድር ውሃ ፍሰት ይኖራቸዋል፡፡ በመሆኑም የሚኖሩ ስጋቶችን ለመቀነስና መልካም አጋጣሚዎች ለመጠቀም ከታች የቀረቡትን ቦታ ተኮር የውሀ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሀሳቦች በተገቢው ሁኔታ መተግበር ያስፈልጋል።

ሠንጠረዥ 3፡ በሚቀጥሉት አስር ቀናት የሚኖረዉ የእርጥበት ሁኔታ በዉሀዉ ዘር ላይ ሊኖር የሚችለው ተጽዕኖ

| የውኃ ተፋሰሶች | የእርጥበት ሁኔታ | አዎንታዊ ተጽዕኖ | አሉታዊ ተጽዕኖ | የውኃ ሚቲዎሮሎጂ ምክረ ሃሳብ |
|---|---|---|---|---|
| በላይኛው እና በመካከለኛ ኦሞ ጊቤ፣ በላይኛው ስምጥ ሸለቆ፣ በመካከለኛ አባይ፣ በጥቂት ላይኛው ገናሌ ዳዋ እና አዋሽ | ከመካከለኛ እስከ ከመጠነኛ | | • አንጻራዊ የትነት መጨመር | • የሚገኘውን ውሃ ከብክነት እና ከብክለት መጠበቅ<br>• ውሃን በተገቢ ሁኔታ ማሰባሰብ |
| በአብዛኛው፣ ተከዜ፣ አዋሽ፣ ዋቢ ሸበሌ፣ ገናሌ ዳዋ፣ አፋር ደናክል፣ መረብጋሽ፣ ኦጋዴን እና አይሻ፣ | ደረቅ ሁኔታ | • የውሃ ብክለት እና የአፈር መሸርሸር አደጋዎችን ይቀንሳል | • የወንዞች የውሃ መጠን መቀነስ | • ዉሃን በአግባቡና በቁጠባ መጠቀም<br>• ውሃ ለአስፈላጊ ፍላጎቶች ብቻ መጠቀም |

Ethiopian Meteorology Institute